# ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ መተዳደሪያ ደንብ

## መግቢያ

ሙስና በዓለም ላይ መከሰት የጀመረው ከመቼ ወዲህ እንደሆነ ተለይቶ የሚታወቅ ባይሆንም ከመንግስት ተቋም መፈጠር ጋር የተያያዘ መሆኑ ግን የሚያጠራጥር አይደለም።

ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ድርጅት በሰጠው አጭር ትርጉም መሰረት ሙስና "ለሕዝብ ማገልገያ የተሰጠውን ሥልጣን ለግል ጥቅም ማዋል" ማለት ነው።

የሙስና ተግባር ዘርፈ ብዙ ሲሆን በማንኛውም መልኩ ሆነ በየትኛውም ቦታና በማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ቢፈፀም ዓላማው ያልተገባ ጥቅምን ለማስገኘት መሆኑ ግልጽ ነው። በዚህም ዓላማ አላግባብ የተወሰነ ወገን ተጠቃሚ ቢሆንም በውጤቱ ወይም በሌላ ጐኑ ግን በሀገርና በህዝብ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ነው።

ሙስና ግለሰብንና ህብረተሰብን ይጐዳል፣ ሙስና የመንግስት ክብር ይቀንሳል፣ ሙስና የሕዝብን ሞራል ይበክላል፣ የህሊና ልዕልና ዝቅ ያደርጋል፣ ብሔራዊ ስሜትን ያዳክማል፣ ልማትን ይጐትታል። በአጠቃላይም በአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ክብር ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል።

ስለሆነም ዛሬ በመላው ዓለም ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችና ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ ድርጅቶች እንዲሁም አብዛኛው የዓለም መንግሥታት ይህንን የሙስና አስከፊ ሂደት ለመግታት ቆርጠው የተነሱበት ወቅት ነው።

ሙስና በሀገራችን ያለው ገጽታ ሲታይ ቀደም ካሉት ጊዜያት ጀምሮ እያደገ የመጣና አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ ችግር መሆኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያ መንግሥትም ከዓለም አቀፍ ሁኔታ ባልተለየ መልኩ ይህንን ወንጀል ለመከላከል ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን በተደጋጋሚ ያሳወቀ ከመሆኑም ሌላ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ሲሆን በቅርቡም የእንምባ ጠባቂ መ/ቤትና የሰብዓዊ መብት አስከባሪ ኮሚሽንን በአዋጅ ለማቋቋም እየወሰደ ያለው እርምጃ የዚሁ ጥረት አካል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ሙስና በመላው የዓለም ሀገሮች በተለያየ መልክና መጠን የሚገኝ ከመሆኑም ሌላ ድንበር ዘለል ጠባይም ያለው በመሆኑ ዓለም አቀፍ ቅንጅት ባለው መልኩም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል። በዚህም መሠረት «ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል» የተባለ ለመላው ዓለም በማዕከልነት የሚያገለግል ከፖለቲካ ዓላማዎች ገለልተኛ የሆነና አትራፊ ያልሆነ የፀረ-ሙስና ድርጅት ተቋቁሞ በመላው ዓለም በተመሳሳይ ዓላማ ላይ የተመሠረቱ

አህጉራዊና ብሔራዊ ማኅበሮች እንዲቋቋሙ ብቻ ሳይሆን አሠራራቸውንም ከዓለም አቀፍ አሠራር ጋር በማቀናጀት ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ይገኛል፡፡

በዚህ ማዕከሉን በጀርመን አገር በበርሊን ከተማ ባደረገው ግዙፍ የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መርህ መሠረት በየሀገሩ የሚቋቋሙት ብሔራዊ ማህበሮች በመንግሥት፣ በሲቪል ህብረተሰብና በግሉ ሴክተር ቅንጅት ላይ የተመሠረቱ መሆን እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡

በመሆኑም ከላይ እንደተጠቀሰው በሀገራችን በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የሙስና አስከፊ ገጽታ ለመለወጥ በመንግሥት በኩል እየተደረገ ያለው ጥረት እንዳለ ሆኖ በሲቪል ህብረተሰቡም በኩል ይህንኑ ዓላማ የሚያራምድና ከዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ንቅናቄ ጋር የዓላማና የአሠራር አንድነት ያለው በህብረተሰባችን ውስጥ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ በአስተዳደር በኩልም ግልጽነት እንዲኖርና እንደሁኔታውም የአሠራር መስተካከል እንዲደረግ የሚጥር በአጠቃላይም የዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ድርጅት የ«ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል» መርሆችን ይዞ የሚራመድ ብሔራዊ የሲቪል ህብረተሰብ ማኅበር ማቋቋም አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ስለሆነም ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ከዚህ በታች በዝርዝር የተገለፀውን ዓላማ ተግባራዊ የሚያደርግ «ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ» ተብሎ የሚጠራ ከፖለቲካ ዓላማ ገለልተኛ የሆነና አትራፊ ያልሆነ ብሔራዊ የፀረ ሙስና የሲቪል ህብረተሰብ ማህበር በፍ/ብ/ሕግ/ቁ 404 እና ደንብ ቁጥር 321/1995 መሠረት የተቋቋመ ሲሆን ጥቅምት 19 1995 በፍትሕ ሚኒስቴር ምዝገባ ቁጥር 929 የተሰጠው የ«ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ» ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ በፍትህ ሚኒስቴር በተሰጠው የማኅበራት ደንብ ቅጽ መሠረት ተሻሽሎ ቀርቧል፡፡

## አንቀጽ አንድ

## መቋቋም

ማኅበሩ በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 404 እና በማኅበራት ምዝገባ ደንብ ቁጥር 321/1959 መሠረት ጥር 24 ቀን 1995 ዓ.ም. ላልተወሰነ ዘመን ተቋቁሟል፡፡

## አንቀጽ ሁለት

## ስያሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ማኅበር «**ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ**» (**TRANSPARENCY ETHIOPIA**) በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ "ማኅበር" ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

## አንቀጽ ሦስት

## ማህተምና አርማ

ማህበሩ ለማህበሩ ሥራ የሚያገለግልና በሕጋዊ ምዝገባ የሚጠበቅ የትራንስፓረንሲ አርማ ሲኖረው ከላይ በአማርኛ ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ ከታች በእንግሊዘኛ (TRANSPARENCY ETHIOPIA) የሚል ማህተምና ዓርማ ይኖረዋል፡፡ ዓርማውም የሚያገለግለው ለማኅበሩ ተግባር ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አራት

## ባህርይ

ማኅበሩ ለትርፍ ያልተመሰረተ፣ ወገናዊ፣ ፖለቲካዊ ያልሆነ ማኅበር ነው፡፡

## አንቀጽ አምስት

## ዋና ጽ/ቤት

የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ አስተዳደር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 111/18 የሚገኝ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ክልሎችም ቅርንጫፍ ቢሮዎችን ይከፍታል፡፡ ስልክ **251-11-5510738 /6555508** ፖስታ ሣጥን ቁጥር **27847/1000**
e-mail tirat.ti@ethionet.et

# <u>አንቀጽ ስድስት</u>

## <u>የማህበሩ ዓላማዎች</u>

1. ዜጐች ሕገ መንግስቱ ያጐናጸፋቸውን መብቶችና ግዴታዎችን ጠንቅቀው እንዲረዱና እንዲጠቀሙ ማሳወቅ፤
2. ሕብረተሰቡ ከሙስና ነፃ የሆነ የባህሪይ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያስችለው ባህል መፍጠር፤
3. የግልጽነትና የተጠያቂነት ባህል በመንግሥት ኃላፊዎችና ማኅበረሰባዊ ተቋማት መሪዎች ዘንድ እንዲሰርፅ ሙሉ ጥረት ማድረግ፤
4. የሙስና ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያገለግሉ ሕጐችን በህብረተሰቡ ዘንድ በቀላሉ ተለይተው እንዲታወቁና እንዲሰርፁ ማድረግ፤
5. የአመለካከት፣ የአስተሳሰብና የሞራል ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ጽሑፎችን በማዘጋጀት በኅብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳይ ለማጋለጥ የሚያስችል ሁኔታዎች መፍጠር፣ ማሠራጨትና ትምህርት መስጠት፤
6. ሕፃናትና ወጣቶች በመልካም ሥርዓት፣ በግብረገብነትና በግልጽነት ታንፀው የሚያድጉባቸው ዘዴዎች መቀየስና ከወዲሁም ሙስና መዋጋት የሚያስችላቸውን ባሕል መፍጠር፤
7. ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከርና በመተባበር የተለያዩ የሕግ ግንዛቤን የሚያዳብሩ ሴሚናሮችና ሲምፖዚየሞችን ማዘጋጀት፣
8. በመንግሥት ሥራና በማህበራዊ አገልግሎት የተሰማሩ ሰዎች (ሠራተኞች) ከሙስና ነፃ እንዲሆኑ ማበረታታትና ጥራት ያለው አገልግሎት ስለመስጠታቸው ማትጊያ ይሆናቸው ዘንድ የሞራልና ቁሳዊ ድጋፍ መስጠት፤
9. ከሌሎች መሰል አገር በቀል አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ማኅበራት ጋር በመስኩ የሥራ ግንኙነትና ትብብር መፍጠር፤
10. የሙስናን መንስኤዎች በማጥናት የመከላከል ዘዴዎችን መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፤
11. የግልጽነትና የተጠያቂነት ባህል በህብረተሰቡና በመንግሥት ኃላፊዎች ዘንድ እና ማኅበራዊ ተቋማት መሪዎች እንዲለመዱ ሙሉ ጥረት ማድረግ፡፡
12. በሀገራችን የሚካሄደውን ምርጫ ነፃ፣ ፍትሀዊ እና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን የበኩሉን ድርሻ በተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 89 እና 90 መሠረት ከቦርዱ ፍቃድ ሲያገኝ የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመራጮች በመስጠት መሳተፍ ወይም በምርጫ ሕጉ አንቀጽ 78 እና 79 መሠረት ከቦርዱ ፍቃድ ሲያገኝ በምርጫው ወቅት መታዘብና በአንቀጽ 81 መሠረት የትዝብቱን ሪፓርት ለቦርዱ የማቅረብና ይፋ የማድረግ፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## አባልነት

ማኅበሩ መደበኛ አባል፣ ተባባሪ አባል ይኖሩታል።

ሀ. **መደበኛ አባል**

ማለት ለአካለ መጠን የደረሰ በአንድ በተለየ የሙያ ዘርፍ በመስራት ልምድ ያካበተና በማህበሩ ህልውና ላይ ከፍተኛ ሚና የሚኖረው የፀረ-ሙስና ትግሉን የሚያግዝ ለመ/ቤቱ ህልውና ብሎም እድገት የበኩሉን ድርሻ ማበርከት የሚችል እንደሆነ በቦርዱ ግብዣ የተደረገለትና አመኔታ ያገኘ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤው ያፀደቀለት ግለሰብ ነው። ይህ አባል የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብና የማህበሩን ቃል ኪዳን የተቀበለ፣ ሙስናን ለመዋጋት ሊያደናቅፉ ከሚችሉ ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነፃ የሆነ እንዲሁም መደበኛ የአባልነት መዋጮን የከፈለ ሆኖ ሊመዘገብ ይችላል።

ለ. ተባባሪ አባል

ማለት ማህበሩ የሚያካሄደውን የፀረ-ሙስና ትግል በሞራል፣ በሙያ፣ በገንዘብና በተለያዩ ቁሳቁሶች በመደገፍ የተሰለፈ ነው። ማንኛውም የማኅበሩን ዓላማ የተቀበለ ሙስናን ለመዋጋት ሊያደናቅፉ ከሚችሉ ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነፃ የሆነ ግለሰብ ተባባሪ አባል መሆን ይችላል።

ሐ. የክብር አባል

ማለት በማኅበሩ ቦርዱ ቀርቦና በጠቅላላ ጉባኤው የፀደቀ በሙያውና በምግባሩ ለፀረ-ሙስና ትግል አርአያ መሆን የሚችል ግለሰብ የማህበሩ የክብር አባል ይባላል። ማንኛውም በሕብረተሰቡ ውስጥ ታዋቂነት፣ ተደማጭነት ያለው፣ በሰነ- ምግባሩ የታወቀ ሙስናን ለመዋጋት ሊያደናቅፉ ከሚችሉ ከማንኛውም ጥቅም ግጭት ነፃ የሆነ ግለሰብ የክብር አባል ሊሆን ይችላል።

## አንቀጽ ስምንት

## የአባላት መብት

1. አባል ለመሆን የሚሹ በማኅበሩ የተዘጋጀውን የአባልነት ፎርም መሙላት ይኖርባቸዋል።
2. ሁሉም አባል እኩል መብት አላቸው።
3. የማኅበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው።

4. ማንኛውም የማኅበሩ መደበኛ አባል፡-
   ሀ. የመምረጥ የመመረጥና ስለማኅበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣
   ለ. በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የመገኘት፣ ስለማኅበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምፅ የመስጠት መብት አለው በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የመገኘት፣ ስለማኅበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምፅ የመስጠት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

## የአባላት ግዴታ

1. ማንኛውም አባል የአባልነት መዋጮውን በወቅቱ መክፈል አለበት፡፡
2. አንድ አባል ከማኅበሩ ሲወጣ ባለው ኃላፊነት የተነሳ የማኅበሩ ገንዘብ በእጁ ገብቶ ከነበረ የሚፈለግበትን ዕዳ ይከፍላል፡፡
3. ማንኛውም አባል የማኅበሩን ዓላማ የማክበርና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
4. የማኅበሩ አቅም ለማጐልበት፣ ዓላማውን ለማሳካትና ለማስፋፋት በሀሳብ፣ በሙያ በጉልበትና በገንዘብ መደገፍ፣
5. ለጋሽ ግለሰቦችና ድርጅቶች ዓላማውን አውቀው እንዲረዱ በሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ፣
6. አንድ አባል የሚጠበቅበትን መዋጮ ካልከፈለ ወይም የሚጠበቅበትን አገልግሎት ካልሰጠ በመብቱ አይሰራበትም፡፡
7. የአባልነት ክፍያ መዋጮ
   - መደበኛ አባል ምዝገባ፡- በዓመት 50.00 ብር / ሀምሳ ብር/
   - የግለሰብ ተባባሪ አባል፡- መመዝገቢያና ዓመታዊ መዋጮ በቦርድ ይወሰናል
   - የክብር አባል ለመመዝገቢያ፡- 500.00 /አምስት መቶ/ ብር በዓመት 100.00/አንድ መቶ/ ብር ነው፡፡
8. ተባባሪና የክብር አባላት ከመምረጥ መመረጥ ሌላ ለሌሎች አባላት የተሰጡት መብትና ግዴታዎች ይኖራቸዋል፡፡

## አንቀጽ አሥር

## አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

አንድ አባል፡-

1. ሲሞት፣ ወይም
2. ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በጠቅላላ ጉባዔው እንዲሰናበት ሲወሰን ወይም
3. በራሱ ፍቃድ በፅሑፍ ሲጠይቅ አባልነቱ ይቋረጣል፡፡
4. አባልነት ሲቋረጥ የአባልነት ክፍያ ተመላሽ አይሆንም፡፡

## አንቀጽ አሥራ አንድ

## የማኅበሩ መዋቅር

ማኅበሩ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው፡፡



## አንቀጽ አሥራ ሁለት

## የጠቅላላው ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

ጠቅላላ ጉባዔ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 7 ላይ የተጠቀሱትን አባላት የሚያካትት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ጠቅላላ ጉባዔ የማኅበሩ የበላይ አካል ነው፣
2. የቦርድ አባላትን፣ ኦዲተሩን፣ የጉባዔውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይመርጣል፣ ይሽራል፣
3. በማኅበሩ የፖሊሲ አቅጣጫ ላይ ውሣኔ ይሰጣል፣
4. ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምን በመመርመር ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፣
5. ዓመታዊ የሥራና የኦዲት ሪፓርት መርምሮ ያፀድቃል፣
6. የማኅበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
7. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በተገለጸው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣
8. ቦርዱ የሚያቀርበውን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በማዳመጥ ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማና የተነደፉ መርሃ ግብሮች ተግባራዊ መሆን አለመሆናቸውን ያረጋግጣል፣
9. መተዳደሪያ ደንቡን ያሻሽላል፣
10. የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚለወጥበት እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚከፈቱበት ሁኔታ ላይ ይወስናል፣
11. የማኅበሩ ሂሣብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣
12. የማኅበሩ መፍረስ ላይ ውሣኔ ይሰጣል፣
13. በሌላ የማኅበሩ አመራር አካል ያልተሰጡ ጉዳዩች ይወስናል፣
14. በጠቅላላ ጉባኤው መሥራች አባላትን፣ የቦርድ አባላትንና ሌሎች የተወከሉ አባላትን ያካትታል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሦስት

## የጠቅላላው ጉባኤ አመራር አካላት ሥልጣንና ተግባር

ጠቅላላው ጉባዔ ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ሥልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፡፡

1. **የጠቅላላው ጉባዔ ሰብሳቢ፣**

ሀ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፣

ለ. ጠቅላላው ጉባዔ የሚያወጣቸው ደንቦችና የሚሰጣቸው ውሣኔዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡

ሐ. ጉባዔው ያፀደቃቸውን የሥራና የኦዲት ሪፖርቶች ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትና ዕርዳታ ለጋሾች (donors) እንዲደርሱ ያደርጋል፣

መ. ለጉባዔ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ፀሐፊው በአጀንዳ ያስይዛል

1. **ፀሐፊው፣**

ሀ. ከሰብሳቢው ጋር በመሆን ለጉባዔው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣

ለ. የጉባዔውን ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፣

ሐ. የጉባዔውን ሰንድ ይይዛል፣

መ. የጉባዔውን ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል

## አንቀጽ አሥራ አራት

## የጠቅላላ ጉባዔ የስብሰባ፣ የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት

1. የጠቅላላው የጉባዔ መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ የሚካድ ሆኖ አስቸኳይ ጉዳዩች ሲያጋጥሙ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
2. ከማኀበሩ አባላት ከ10% በላይ በሚሆኑ ጥያቄ የጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. ጉባዔው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ ሦስት የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፡፡
4. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፡፡
5. የማኀበሩ መደበኛ አባላት 51% ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፣ ይህ ሣይሟላ ቀርቶ ሁለተኛ ጥሪ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በአግባቡ ለአባላት መድረሱ ሲረጋገጥ አባላት በተገኙበት በጥሪው ላይ በተገለጸው አጀንዳ ላይ ብቻ ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
6. የአባላት ቁጥር ከመብዛታቸው የተነሳ የማኀበሩን አባላት በሙሉ መሰብሰብ ካልተቻለ በውክልና መሰብሰብ ይቻላል፡፡ የአወካከሉ ስርዓት በማኀበሩ የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡
7. የጉባዔው ውሣኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው በተገኙ አባላት ድምፅ ብልጫ ሆኖ እኩል ድምፅ ሲኖር ሰብሳቢው የደገፈው ሃሳብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አምስት

## የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርድ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

1. የማኅበሩን ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ይሽራል፣
2. በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡ ውሳኔዎችንና የሚወጡ እቅዶች በሥራ አስኪያጁ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፡፡
3. የማኅበሩን ፖሊሲ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የማኅበሩ ማኔጅመንት የሚያቀርባቸውን ሀሳቦች ተቀብሎና አስፈላጊም ሲሆን የራሱን አስተያየት ጨምሮ ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ለጉባዔው ያቀርባል፣
4. በገንዘብ ወይም በማቴሪያል ለማኅበሩ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ገቢዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፣ ዕርዳታ የሚገኝበትንም መንገድ ይቀይሳል፣
5. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ ያስወስናል፣
6. ከማኅበሩ ማኔጅመንት የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፣
7. ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣
8. በማኅበሩ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጀት ላይ በመምከር ለጠቅላላው ጉባዔ ያቀርባል፣
9. የሥራ አመራር መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች የውስጥ ደንቦች ያወጣል፣
10. አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የሚጠራበት ምክንያት ሲያጋጥም ጥሪ እንዲደረግ ይወስናል፡፡

## አንቅጽ አሥራ ስድስት

## የሥራ አመራር ቦርድ አባላት

1. የሥራ አመራር ቦርድ 9 /ዘጠኝ/ አባላት ይኖሩታል፣
2. ቦርዱ ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ይመርጣል፣
3. የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፡፡

4. ሰብሳቢ፣

   ሀ. የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፣

   ለ. ቦርዱ በስብሰባ ያሳለፋቸውን ውሣኔዎች ለጠቅላላው ጉባዔ ያቀርባል፣

   ሐ.ቦርዱ የሚያወጣቸውን የማኅበሩን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ለጠቅላላው ጉባዔ አቅርቦ ያፀድቃል፣

   መ.ለጠቅላላ ጉባዔውና ለቦርዱ ከተሰጠው ሥልጣን አንፃር ተጠሪነቱ ለጉባዔውና ለቦርዱ ይሆናል፣

   ሠ. ጠቅላላው ጉባዔና ቦርዱ የሚያሳልፏቸው ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ሥራ አስኪያጁን ያዛል፣

   ረ. የማኅበሩን ማኔጅመንት የሥራ አፈፃጸም በቅርብ ይከታተላል፣

   ሰ. ጉባዔው ያጸደቀውን የሥራ አፈጻፀምና የኦዲት ሪፖርት ለሚመለከታቸው እንዲልክ ሥራ አስኪያጁ ያዛል፣

   ሸ. ከኦዲት ሪፖርት ውጭ ያሉትን ዓመታዊ ሪፖርቶች በጉባዔው መደበኛ ስብሰባ ያቀርባል።

5. ምክትል ሰብሳቢ፣

   ሀ. ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ ይሠራል፣

   ለ. በሰብሳቢው የሚሰጠውን ተጨማሪ ሥራ ያከናውናል።

6. ፀሐፊ፣

   ሀ. ተጠሪነቱ ለቦርዱ ነው፣

   ለ. የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፣

   ሐ. የቦርዱን ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፣

   መ. የቦርዱን ጽ/ቤት መዛግብትና ሠነድ ይጠብቃል።

## አንቀጽ አሥራ ሰባት

## የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ፣ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት፣ የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን፣

1. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በዓመት 12 ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም በማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሊጠራ ይችላል፣

3. ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፣ ድምፅ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ሃሳብ ይጸናል፡፡
5. የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን 3/ሦስት/ ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ከቦርዱ አባላት ውስጥ በሦስተኛው አመት ምርጫ አምስቱ /5/ በድጋሚ መመረጥ ሲችሉ በስድስተኛው /6/ ዓመት ምርጫ ደግሞ 4ቱ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ የቦርድ አባል በተከታታይ ከ 2 /ሁለት/ ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፣
6. የቦርድ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፡፡

## አንቀጽ አሥራ ስምንት

## የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

የማኅበሩ ሥራ አስኪጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. በማናቸውም አካል ዘንድ ማኅበሩን ይወክላል፣ የማኅበሩን ሥራ በተመለከተ ማናቸውንም ጉዳዮች ይፈጽማል፣ ውክልና ይሰጣል፣ በማኅበሩ ስም የደብዳቤ ልውውጦችን ያደርጋል፣ ውል ይዋዋላል፡፡
2. በማኅበሩ ስም የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡
3. በጠቅላላው ጉባዔና በቦርዱ የሚተላለፉ ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
4. የማኅበሩን የየሦስት ወር እና ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርቶች እያዘጋጀ (በየሶስት ወሩ እና በየዓመቱ) ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
5. የማኅበሩን ፖሊሲ በማውጣትና የበጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ማኅበሩ ገቢ የሚያገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ የማኅበሩን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ስልቶችን በመቀየስ ያስፈጽማል፡፡
7. ቦርዱ በሚያወጣው የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስናብታል፣ ደመወዛቸውንና አበላቸውን ይወስናል፡፡
8. ከሂሳብ ሹሙና ከገንዘብ ያዥ የሥራ ኃላፊነቶች ውጭ ያሉትን የሥራ ድልድሎች በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
9. ሂሣብ ሹሙና ከገንዘብ ያዡ ጨምሮ፣ በሥሩ የሚገኙትን ሠራተኞች እያስተባበረ፣ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የማኅበሩን የዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡

10. የማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሌሎች የማኔጅመንት ውሣኔዎች ይሰጣል፡፡
11. ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩ አባል ከሆነ ሀሳቡን ለማፅደቅ ወይም በኃላፊነቱ የተከናወነውን ለማጽደቅ በሚደረገው ጠቅላላ ጉባዔ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡
12. የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ወይም የጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔን በማይቃረን ሁኔታ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ዘጠኝ

## የማኅበሩ ሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሂሳብ ሹሙ ተጠሪነቱ ለማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የማኅበሩን ሂሣብ ገቢና ወጪ ይቆጣጠራል፣ በትክክል እንዲመዘገብና እንዲያዝ ያደርጋል፡፡
2. የማኅበሩ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሳብ አሠራር ደንብ መሠረት መሆኑን ይቆጣጠራል፡፡
3. የማኅበሩን የባንክ እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሥራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡
4. የማኅበሩ የሂሳብ መዛግብትና የተለያዩ ሠነዶች በጥንቅቄ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ

## የማኅበሩ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

ገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የማኅበሩን ገቢዎች በሕጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፣
2. የተሰበሰበውን ገንዘብ ባንክ ገቢ ያደርጋል፣ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣
3. ለሥራ ማስኬጃና ለማኅበሩ ጥቃቅን ወጭዎች የሚሆን ከብር 5000/አምስት ሺ/ ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፣

4. ከሂሣብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሂሳብ በየወሩ ያመሳክራል፣
5. የማኅበሩን ቼክ ይይዛል፣
6. በጣምራ ፊርማ/በሂሳብ ሹሙና በሥራ አስኪያጁ/ ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ

## የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላው ጉባዔ ሆኖ፣ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የማኅበሩን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣
2. የማኅበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣
3. ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሁለት

## የማኅበሩ የገቢ ምንጭ

የማኅበሩ የገቢ ምንጮች፣

1. የአባላት መዋጮ፣
2. ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሦስት

## የበጀት አመት

የማኅበሩ የበጀት አመት እ. ኤ. አ. ከጥር 1 ------------ ዓ.ም. እስከ ታህሣሥ 31 ---------- ዓ.ም. ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አራት

## የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔው ¾ ድምፅ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት

## ስለማኅበሩ መፍረስ

1. የጠቅላላ ጉባዔ አባላት ማኀበሩ እንዲፈርስ በ3/4 ድምፅ ከወሰኑ፣
2. ማኀበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ከፍፃሜ ሲያደርስ ወይም ከፍፃሜ ለማድረስ ሳይቻለው ሲቀር ሊፈርስ ይችላል፡፡
3. ማኀበሩ በሚፈርስበት ጊዜ ንብረቱ ተመሳሳይ ዓላማ ላለው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ለመንግሥት ይተላለፋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስድስት

## መተዳደሪያ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ ሥልጣኑ በሚፈቅድለት የመንግስት አካል ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ይህ የተሻሻለው መተዳደርያ ደንብ በሆርን ኦፍ አፍሪካ ፕሬስ ኢንስቲትዮት አዳራሽ በተደረገው የጠቅላላ ጉባዔ መጋቢት 1 ቀን 1999 ዓ.ም ፀድቋል፡፡